10ኛ ዓመት ቁጥር 59
10th Year No.59

ባህር ዳር ሐምሌ 20 ቀን 1997 ዓ.ም
Bahir Dar 27 July, 2005

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ
# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር **118/1997** ዓ.ም

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የግብርና ምርምር ተቋም ማቋቋሚያ

አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ

## in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ
መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት
የወጣ

**Issued under the auspices of the Council of the Amhara**

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 32.05
Unit price ------

### አዋጅ ቁጥር 118/1997 ዓ.ም

### የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የግብርና ምርምር ተቋምን ማቋቋሚያ አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በሀገሪቱ የገጠር ልማት ፖሊሲ መሰረት የክልላችን የግብርና ምርምር ሊያተኩርባቸው የሚገቡ ጉዳዩችን በግልጽ መለየትና ተልኮውን መወሰን በማስፈለጉ&

ተቋሙ በተደራጀበት አዋጅ መሰረት ልማቱን የሚደግፍ ቴክኖሎጂዎችን ከማፈላለግና ከክልሉ ተጫባጭ ሁኔታዎች ጋ ከማላመድ አልፎ በቴክኖሎጂ ብዜት ላይ ጭምር እንዲሰማራ የተፈቀደለት አሰራ የምርምሩን የትኩረት አቅጣጫ እንደሚያዛባ ስለታመነበትና ይኸው ኃላፊነት በሌላ ህግ ለክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የተሰጠ በመሆኑ&

የተቋሙን ዓላማ አግባብ ባላቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ የተመሰረተ እንዲሆን አድርጎ እንደገና መቅረጽና የማስፈፀሚያ አደረጃጀቱንም ለተልዕኮው መሳካት በሚበጅ አግባብ ማሻሻል ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ&

የአማራ ብሄራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 49 አንቀጽ 3/1 ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል::

**1.** <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የግብርና ምርምር ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 118/1997 ዓ.ም " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. <u>ማሻሻያ</u>

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የግብርና ምርምርም ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 48/1992 ዓ.ም እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

ሀ. የአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3 ተሰርዞ ከዚህ በታች በተመለከተው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ተተክቷል::

**3**. "የግብርና ምርምር ማዕከላት " ማለት ተቋሙ ተግባሩን ለመፈፀም ይቻለው ዘንድ አጥንቶ ለቢሮው የሚያቀርባቸውና በክልሉ መንግስት ዕውቅና የተደራጁና ወደፊት የሚደራጁ የምርምር ማዕከላት ናቸው::

ለ. በአዋጁ አንቀጽ 2 ስር ከንዑስ አንቀጽ 5 ቀጥሎ ከዚህ በታች የተመለከቱት አዲስ ንዑስ አንቀጽ 6 እና 7 ታክለዋል::

6. ″ቢሮ″ ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የግብርናና ገጠር ልማ ልማት ቢሮ ነው፡፡

7. ″የግብርና ቴክኖሎጂ″ ማለት የግብርና ልማትና ለማፋጠን የሚረዱ ማቸውም መሳሪያ' የዕፅዋት' የእንስሳትና የደን ዛፍ ዝርያዎች' የተሻሻሉ የግብርና አሰራሮች' ዘይቤዎችና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡

ሐ. የአዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 ተተክቷል፡፡

2. የተቋሙ ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና ለቢሮው ይሆናል፡፡

መ. የአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1. የመንግስትን ልማት ፖሊሲዎች በማስፈፀም የክልሉን ህዝብ ኑሮ ለማሻሻል ይቻል ዘንድ ለግብርና ልማት መፋጠን ማነቆ የሆኑ ችግሮችን መለየትና እነዚህንም ለማቃለል በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር ተግባር ላይ ውለው ውጤት ያገኙ መፍትሄዎችን በማምጣትና በክልሉ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማላመድ የመነሻ ቴክኖሎጂዎች ወይም ናሙናዎችን ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጩ ማዘጋጀት፡፡

ሠ. የአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች እንደሚከተለው ተሻሽለዋል፡፡

1. የግብርና ምርምር አማካሪ ቦርድ ከዚህ በኋላ ″ቦርድ″ እየተባለ የሚጠራ&



2. በቢሮው አቅራቢያ በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተር' ምክትል ዋና ዳይሬክተርና ዳሬክተሮች፡፡

ረ. የአዋጁ አንቀጽ 6 ተሰርዞ ከዚህ በታች በተመለከተው አዲስ አንቀጽ 6 ተተክቷል፡፡

**6.** <u>ስለቦርዱ አባላት</u>

ቦርዱ ሰብሳውን ጨምሮ በቢሮ ሃፊው የሚሰየሙ ከ 5 እስከ 7 አባላት ይኖሩታል፡፡

ሰ. የአዋጁ አንቀጽ 7 ሙሉ በሙሉ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 7 ተተክቷል፡፡

## 7. <u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ ተጠሪነቱ ለቢሮው ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ተቋሙ የሚያካሄደው ምርምር በመንግስት የፖሊሲ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ስለሚሆኑ ይገመገማል' አዳዲስ ጠቃሚ የምርምር ሃሳቾን ላማመንጨት የሚስችሉ ስልቶችን ይነድፋል' ምርምር እንደካሄድባቸው በየጊዜው አቅጣጫ ይሰጣል'
2. የተቋሙን ዓላማ ለማሳካት በሚረዱ ሌሎች ጉዳዩች ላይ ያማክራል' ሃሳብ ያቀርባል'
3. የራሱን የውስጥ ደንብ አዘጋጅቶ በቢሮው ሲፀድቅለት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

ሸ. የአዋጁ አንቀጽ 9 ተሰርዞ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

## 1. የተቋሙ ስልጣንና ተግባር

ተቋሙ ቀጥሎ የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. በአገሪቱ የሳይንስና ቴክኖሎጂ' የግብርና ልማትና ምርምር ፖሊሲዎች መሰረት የክልሉ የግብርና ምርምር ማስተር ፕላን ተግባራዊ ለማድረግ የምርምር ቅደም ተከተል መወሰን' የስራ ፕሮግራምና እቅድ ማውጣት' በክልሉ መንግስት ሲፀድቅም ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም በሚመለከታቸው ተግባራዊ መሆኑን መከታተል&

2. የክልሉን የግብርና ምርምር ፖሊሲ መንደፍ' የማሻሻያ የፖሊሲ ሃሳብ በማመንጨት ማቅረብና ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ&

3. በግብርና ላይ ተሰማርቶ የሚገኘውን ህብረተሰብ በተነፃፃሪ አጭር ጊዜ ውስጥ ከድህነት ለማውጣትና ወደ ላቀ የኢኮኖሚ ደረጃ ለማሸጋገር የሚያስችሉ' የተለያዩ የስነ-ምህር ቀጠናዎችን መሰረት ያደረጉና በማላመድ ላይ የተመሰረተ አግባብን በጥብቅ በመከተል የሚቀረፁ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ማዘጋጀት&

4. የክልሉ የልማት ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ የግብርና ምርምር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን ለመቅረፅና ለማዘጋጀት የሚያስችል መመሪያ ማውጣት' በአግባቡ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በጀት መገምገምና በመመሪው መሰረት መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ&

5. በክልሉ የግብርና ምርምር ፖሊሲና ስትራቴጅ መሰረት የግብርና ምርምር ማከናወን ወይም እንዲከናወን ማድረግ&

6. በክልሉ ውስጥ የተለያዩ የግብርና ምርምር ማዕከት የሚቋቋሙበትንና የሚደራጁበትን ሁኔታ በየጊው እያጠና ለቢሮው ማቅረብና ሲፈቀድም በተግባር ላይ ማዋል& በክልሉ የግብርና ምርምር ማስተር ፕላን ላይ በመመርኮዝ ማንኛውንም በተቋሙ ስር የሚተዳደር የግብርና ምርምር ማዕከል አደረጃጀት በየጊዜው መገምመገም በአዲስ መልክ እንዲደራጅ ወይም እንዲታጠፍ ለቢሮው ሃሳብ ማቅረብና ሲወሰንም ተግባራዊ ማድረግ&

7. የግብርና ተመራማሪዎችን ለበለጠ ውጤት የሚነሳሱ አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር' አርሶ አደሮች ዘንድ ደርሰው ባስገኙት ተጨባጭ ለውጥ ላይ በዋናት የሚመሰረቱ የዕድገት መሰላሎችን ማዘጋጀት ሲፈቀድም በተግባር ላይ ማዋል&

8. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የህብረተሰቡን የግብርና ዕውቀት አድማስ ለማስፋት በምርምር የተገኙ

ውጤቶችን ማስተዋወቅ' አመቺ የሆኑ የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም ተገቢውን ተግባር ማከናወን&

9. በክልሉ' በአገር ውስጥና በውጭ አገር በተካሄዱና በሚካሄዱ የግብርና ምርምሮችና የምርምር ውጤቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን በማሰባሰብ ማከማቸትና ማሰራጨት' የመረጃ ቅብብሎሽ ስርአትን መገንባትና መምራት&

10. በክልሉ ግብርና ምርምር ላይ የሚሰማራ ብቃት ያለው የሰው ኃይል ለማፍራትና ያለውንም ለማሻሻል በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ተሳትፎ ማድረግ' በተቋሙ የተሰማራውንም የሰው ኃይል አቅም ማሳደግና መገንባት የሚስችል ስልት መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ፡፡



11. በክልሉ ግብርና ምርምር የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ ሰዎች ወይም ተቋሞች ሽልማት የሚሰጥበትን ስርዓት መዘርጋት' ሽልማት ወይም ማበረታቻ መስጠት&

12. በግብርና ምርምር መስክ የተቋቋሙትን ወይም የሚቋቋሙትን የሙያተኞች ማህበራ ማበረታታት እንዲሁም ለፍብርናው ምርምር በመረጃዎች ልውውጥ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት&

13. አግባብ ባለው ህግ መሰረት በሃገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከሚገኙ የግብርና ምርምርና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም ጠቃሚ ድጋፍ ሊሰጡ ከሚችሉ ሌሎች አካላት ጋር ግንኙነቶችን መመስረትና በቢሮው ዕውቅና የትብብር ስምምነቶችን መፈራረም&

14. የክልሉን ግብርና ምርምር በሚመለከቱ ማናቸውም ጉዳዩች ላይ መሳተፍና የክልሉን መንግስት ማማከር&

15. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉና በፌዴራሉ የግብርና ምርምር ማዕከላት አማካኝነት በሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶች መካከል አስፈላጊ ያልሆኑ የስራ ድግግሞሽና የሃብት መባከን እንዳይከሰት ለመከላከል የሚያስችል የፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት&

16. በክልሉ ውስጥ በግብርና ምርምም ስራ ላይ የተሰማሩን ወይም የሚሰማሩን ማንኛውንም ሰው መዝግቦ ዝርዝሩን መያዝ' ስታንዳርድ በማውጣት ስራን መከታተልና የምርምር ጥራቱን መቆጣጠር&

17. የንብረት ባለቤት መሆን' ውል መዋዋል' መክሰስና መከሰስ&

18. ለቢሮውና ለሚመለከታቸው አካላት በየወቅቱ የስራ አፈፃፀምሪፖርት ማቅረብ&

19. ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራን ማከናወን፡፡



ቀ. የአዋጁ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2'3'4'5'7 እና 8 ድንጋጌዎች ተሰርዘው ከዚህ በታች በተመለከቱት አዳዲስ ንዑሳን አንቀጾች ተተክተዋል፡፡

2. የተቋሙንና የግብርና ምርምር ማዕከላቱን በጀት ያዘጋጃል' ለቢሮው ያቀርባል' ሲፈቀድም ስራ ላይ ያውላል&

3. አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተመራማሪዎችን ይቀጥራል' ያስተዳድራል&

4. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ተቋሙን ይወክላል&

5. የተቋሙን የስራ አፈፃፀምና ሂሳብ ሪፖርቶች አጠናክሮ ለቢሮውና አግባብ ላላቸው ሌሎች አካት በየወቅቱ ያቀርባል&

7.በቢሮው የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል&

8.ለተቋሙ ስራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌሎች የበታች የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል&

በ. የአዋጁ አንቀጽ 11 ተሰርዞ ከዚህ በታች በተመለከተው አዲስ አንቀጽ ተተክቷል፡፡

**11.** ነባር የምርምር ማዕከላት ስለሚተዳደሩበት ሁኔታ**፡-**

1. ቀደም ሲል የተቋቋሙት የክልሉ ግብርና ምርምር ማዕከላት በተቋሙ ስር መተዳደራቸውን ይቀጥላሉ&
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም እስካሁን ድረስ በተቋሙ ስር የነበሩት የቴክኖሎጂ ብዜት ማዕከላት ከተቋሙ ወጥተው በቢሮ ስር ይደራጃሉ&

3. የምርምር የብዜት ስራዎችን አጣምረው ሲሰሩ የነበሩ ማዕከላት ስለሚተዳደሩበት አግባብ ቢሮው ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

ተ. የአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 5 ሙሉ በሙሉ የተሰረዘና ንዑስ አንቀጽ 6 የነበረው ንዑስ አንቀጽ 5 ሆኖ የተስተካከለ ሲሆን አንቀጽ 1 እና 4 ድንጋጌዎች በሚከተለው አኳኋን ተሻሽለዋል፡፡

1. የውስጥ አስተዳደር ነፃነት ኖሯቸው በተቋሙ በኩል የሚሰጣቸውን ተልዕኮ መሰረት በማድረግ የመንግስትን ፖሊሲ የተከተሉ የግብርና ምርምር ተግባራትን ማከናወን&

4.የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ የስራ ፕሮግራሞችን አዘጋጅቶ ለተቋሙ ማቅረብና ሲፈቀድላቸው በተግባር ላይ ማዋል፡፡

ቸ. የአዋጁ አንቀጽ 13 ድንጋጌ ሙሉ በሙሉ የተሰረዘ ሲሆን በዚሁ ምክንያት ከአንቀጽ 14 18 ያሉት ድንጋጌዎች አንቀጽ 13'14'15'16' እና 17 ሆነው ተስተካክለዋል፡፡

## 3. <u>አዋጅ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር

ሐምሌ 20 ቀን 1997 ዓ.ም

ዮሴፍ ረታ

የአማራ ብሄራዊ ክልል

| ፕሬዚዳንት | |
|---|---|
| | |